# በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

## የ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ

ሐምሌ/ 2007 ዓ.ም

## ክፍል አንድ


1.መግቢያ ..... 3
1.1. የኢትዮጵያ ራዕይ ..... 2
1.2. የኤጀንሲው ራዕይ ..... 2
1.3. የኤጀንሲው ተልኮ ..... 3
1.4. የኤጀንሲው እሴቶች ..... 3
1.5. የኤጀንሲው የስልጣን ወሰን ..... 5
1.6. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት ..... 5
1.7. የሁኔታዎች ግምገማ ..... 6
1.7.1. ውስጣዊ ጠንካራ ጐኖች ..... 6
1.7.2. ውስጣዊ ደካማ ጎኖች ..... 7
1.7.3. ዉጫዊ ሁኔታዎች ..... 8
ሀ/ ምቹ ሁኔታዎች ..... 8
1.8.የዕቅዱ አፈጻፀም አቅጣጫዎች፤ ..... 8
ክፍል ሁለት ..... 10
2.ቁልፍ ተግባር ..... 10
2.2. አበይት ተግባራት ..... 15
2.2.1. ምዝገባ፣ ፈቃድና እድሳት እንዲሁም በህጉ የተቀመጡ ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት . 15
2.2.2 የዴስክና የመስክ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ..... 16
2.2.3 የንብረት ማጣራት፣ ማስተላለፍና የማስወገድ ተግባር ..... 18
2.2.4. የሕግ አገልግሎት መስጠት ..... 20
2.2.5 የኮሙኒኬሽን ሥርዓትን ማጠናከር ..... 21
2.2.6. የዕቅድ፣ ፋይናንስና ግዥ ማጠናከር ..... 24
2.2.7. የንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ..... 27
2.2.7 የውስጥ ኦዲት አገልግሎትን ማጠናከር ..... 27
2.2.8. የሰው ኃብት ልማት ተግባራት ማከናወን፣ ..... 29
2.2.9. የሴቶች፣ ህፃናትና የወጣቶችን ጉዳይ ..... 30
2.2.10. የኤጀንሲውን ዘርፈ ብዙ ተግባራት ..... 31
ክፍል ሦስት ..... 34
3.1. የክትትል፣ ድጋፍ እና የግንኙነት ሥርዓት ..... 34

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

በሀገራችን የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት የሀገሪቱን ህግ አክብረው በመስራት ለተጀመረው ልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት 2001 ዓ.ም ተቋቁሞ ሀገራችን የነደፈችውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለማሳካት የበኩልን አስተዋጾ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም መሰረት በሀገራችን የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጐት ድርጅቶችና ማኅበራት የሀገሪቱን ህግ አክብረው በመስራት ለተጀመረው የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያበረክቱ ኤጀንሲው በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመደገፍና በመከታተል የህዝቦችን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ጥራት ያለው ለማድረግ የለውጥ ፕሮግራሞችን በማስቀጠል ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ኤጀንሲው የ2007 በጀት ዓመት የሥራ አፈፃፀም በመገምገም  በአፈፃፀም ወቅት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም አመራሩና ሠራተኛው ከተሰጣቸው ኃላፊነትና የስራ ድርሻ አንፃር የታዩባቸውን ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመገምገም መስተካከል ያለባቸውን ጉድለቶች ለማረምና ለመፍታት የጋራ አቋም ተይዟል፡፡ በዚህም መሠረት በ2008 በጀት ዓመት የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የግብዓት፣ የአሰራርና የአደረጃጀት ማነቆዎችን በመፍታት ተልዕኮን በተሟላ መልክ መፈፀም የሚችል የለውጥ ሠራዊት ተከታታይነት ባለው መንገድ በመገንባት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት በቀጣይ በጀት ዓመት አመርቂ የዕቅድ አፈፃፀም ለማስመዝገብ የተቋሙን የ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

### 1.1. የኢትዮጵያ ራዕይ

በህዝብ ተሳትፎ እና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ማህበራዊ፣ ፍትህ የነገሰባት ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያ እውን ማድረግ ነው፡፡

### 1.2. የኤጀንሲው ራዕይ

በ2012 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ውጤታማ የልማት አጋር ሆነው የተጠቃሚዎቻቸውን፣ የአባላቶቻቸውንና የህብረተሰቡን ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ ተረጋግጦ ማየት ነው፡፡

## 1.3. የኤጀንሲው ተልዕኮ

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተደራጅተው በአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት፣ ልማትና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዉስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ በመመዝገብና ፈቃድ በመስጠት እንዲሁም በመከታተልና በመደገፍ የህብረተሰቡ የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነዉ፡፡

## 1.4. የኤጀንሲው እሴቶች

### *ግልፅነትና ተጠያቂነት*

*ግልፅነት ማለት ህዝቡ በመንግስት ፖሊሲዎች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎች የተቋማት አሰራሮችና የመሳሰሉት ላይ ሁልጊዜም ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ ነዉ፡፡ ግልጸኝነት ሲኖር አዳጊ አስተሳሰቦች፣ ፈጣን ውሳኔዎችና ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ በግለሰብ፣ በሙያና በተቋም ደረጃ እየጐለበተ ይሄዳል፤ ግልጸኝነት ሁሉም ሰው የሚመስለውን ሐሳብ የድርሻውን ሳይሸማቀቅ እንዲያበረክት እድል በመፍጠር ጊዜንና ገንዘብን ይቆጥባል፤ ውጤታማነትና ቅልጥፍናን ያሰፍናል፤ ድብብቆሽን በማስቀረትና ሐሜትን በማስወገድ ፊት ለፊት መገነባባትን ይፈጥራል፡፡ ይህም ግላዊ፣ ሙያዊና ተቋማዊ ውጤትን በማሳካት የተቋማችንን ተልእኮ ለማስፈጸምና ለመፈጸም ያበቃናል፡፡ ስለዚህ ሁሉም የተቋማችን  አመራርና ፈጻሚ ባለሙያ ግልጸኝነትን እንደ መሳሪያ መታጠቅ ይጠበቅበታል፡፡*

### የህግ የበላይነትን ማክበር

*የህግ የበላይነት መሠረታዊ የዴሞክራሲ መርህ እንደመሆኑ ይህ መርህ የሕጐች ሁሉ የበላይ ህግ ለሆነው ሕገ-መንግስቱ መገዛትንና ሌሎች መንግስት ያወጣቸውን ህጎች ማክበርና ማስከበርን ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ይህ መርህ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት  አዋጅን፣ ደንብንና መመሪያዎችንና አሰራርን መረዳትን፣ መፈፀምንና ማስፈፀምን ያመለክታል፡፡*

### *መማማርና በቡድን መስራት*

*በአሁኑ ያለንበት 21ኛ ክፍለ ዘመን የውድድር፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችና አሰራሮች በየጊዜዉ የሚፈልቁበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ፈጣንና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ተቋማችን ሳያቋርጥ በመማር ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት ከስራ አፈጻጸም ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ጥናቶችን በማካሄድ ሁሌም ለመማርና ለመሻሻል ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል፡፡ በአጠቃላይ የአመራሩንና የሠራተኛውን እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ የአቅም ዉስንነቶች በትምህርትና በሥልጠና በየጊዜዉ ማጎልበት ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ወዘተ የሚገለፅ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በተመደቡበት የሥራ*

መደብ እውቀትን፣ ክህሎትንና አመለካከትን በሥራ መግለፅና ተጨባጭ ውጤትን በማስመዝገብ ለሕዝብ ጥቅም ሁሉም ፈፃሚና አመራር የሚሰራ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በኤጀንሲው ውስጥ ሊከናወኑ የታቀዱ ሥራዎች ተግባር ላይ የሚውሉት በግልና በጋራ በሚደረግ ጥረት ነው፡፡ በመሆኑም በቡድን ስራ የሚገለፁ ስራዎችን በአገልጋይነት ስሜት እና በጋራ በመሥራት በተጠያቂነት፣ በውጤታማነትና በቅልጥፍና መፈጸም የሚጠበቅበት መሆኑን በአግባቡ መገንዘብ ይገባል፡፡ በተገቢው ውጤት የማያስመዘግቡ እና ከተቋማዊ ስኬት ይልቅ የግል ጥቅምን የሚያስቀድሙ አመራርና ፈፃሚ ባለሙያዎች በየጊዜው በሚደረግ ግምገማ በደረጃ እየተለዩ የእውቅና፣ የግንባታና የማስተካከያ ስራዎች እንዲሰሩ ሁሉም ይረባረባል፡፡

**ብልሹ አሠራርንና ሙስናን መጠየፍ**

የሙስና ምንጩ አንዱ አመለካከት ሲሆን ሙስና ልማትን የሚገትት፣ ሰላምን የሚሸረሽር፣ ተገልጋይና ባለድርሻ አካላት በኤጀንሲው ላይ ያላቸውን እምነት የሚያሳጣ በመሆኑ ይህንን የልማት አረንቋ የሆነውን የሙስና አመለካከትና ድርጊቱን በመጠየፍ መርሆውን በተግባር ላይ ለማዋል እንደ አንድ እሴት ተመርጧል፡፡ በስነ-ምግባር ዙርያ ከተገልጋዮች ጋር በየጊዜው ውይይት ማድረግ እና ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት እራስን ነፃ በማድረግ በኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት ላይ ትግል ይደረጋል፡፡

## 1.5. የኤጀንሲው የስልጣን ወሰን

ሀ/ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ወይም የአባላት ጥንቅራቸው ከአንድ ክልል በላይ በሆኑ ማህበራት፤

ለ/ በአንድ ክልል ብቻ የሚሠሩ ቢሆንም በውጭ አገር በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፤

ሐ/ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት

## 1.6. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት

በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ፈቃድ መስጠት፣ መመዝገብና መቆጣጠር፤

ለ/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የተሻለ አሠራር እንዲኖራቸው ማበረታታት፣

ሐ/ ከሥልጣንና ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ማሰባሰብ፣ መተንተን ማሰራጨት፤

መ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ምዝገባ በሚመለከት መረጃ በጋዜጣ ማሳተምና

ማሰራጨት፤

ሠ/ የመንግሥት አካላት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚሳተፉባቸውን የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፤

ረ/ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችል የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

ሰ/ ለምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ጉዳይ ከሚመለከተው  ዘርፍ አስተዳዳሪ ጋር በመመካከር መርምሮ መወሰን፤

ሸ/ በአዋጅ ቁጥር 334/1995 (እንደተሻሻለ) ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዘለቄታ በጎ አድራጎት እና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሰነዶችን ማረጋገጥና መመዝገብ፣

ቀ/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚጸድቀው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፤

በ/  የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

ተ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በውክልና መስጠት፤ እና

ቸ/ ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም፤

## 1.7. የሁኔታዎች ግምገማ

### 1.7.1. ውስጣዊ ጠንካራ ጐኖች

- ተቋማዊ ተልእኮን ለማሳካት አመራሩና ሰራተኞችን በየደረጃው በማሳተፍና ግልፀኝነት በመያዝ አቅዶ ወደ ስራ መግባቱ፤
- የውጤት ተኮር ምዘና ስርአትን ተግባራዊ በማድረግ  የተከናወኑ ተግባራትን ከጊዜ፣ ከመጠንና ከጥራት አንፃር መለካት መጀመሩ፤
- የተቋሙን የስራ ስፋትና የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ለማጣጣም አደረጃጀት ተጠንቶ ተግባራዊ መደረጉ፣
- የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ቀጣይነት ባለው መልኩ በየስራ ሂደቱ ስራዎችን በቡድን በመስራት እንዲሁም በስራ አመራር ካውንስሉ በየሁለት ሳምንቱ በሚደረጉ የስራ አፈፃፀም ግምገማዎች ላይ በመፈተሽ  የመተጋገል ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ እየተከናወነ መሆኑ፤
- በመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በበጀት አመቱ ዕቅድ እንዲሁም እነዚህን ውጤታማ ማድረግ የሚችሉ የሪፎርም መሳሪያዎች ላይ የተቋሙ ባለሙያዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው መደረጉ፤

- የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ ለተገልጋዮች መሰራጨቱና በስታንደርዱ መሰረት አገልግሎት መስጠት መጀመሩ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ተቋማዊ ተልዕኮ የማሳካት እንቅስቃሴ መጀመሩ፤
- ለህዝብ ክንፍ፣ ለበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ለባለድርሻ አካላት ጋር በአደረጃጀት፣ በአዋጁ፣ በመመሪያዎችና በኤጀንሲዉ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የ1ኛ ዙር አፈፃፀምና የ2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ የጋራ ምክክር መድረክ መደረጉ፤
- በተቋሙ ስርዓተ ፆታ የማስረጽ ተግባራት በመከናወኑ የሴት ሰራተኞች ተሳትፎ መጎልበቱ፤
- በተቋሙ የሴኩላሪዝም መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑ፤
- የአመራር እርከኖች ተለይተዉ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ተዘርግቶ ከተቋም ስራ አመራር ካዉንስል ጀምሮ እስከ ቡድን ተዋቅሮ ስራዎች በግልፅነትና በተጠያቂነት እየተከናወነ መሆኑ፤
- ከደንበኞች በጠንካራና በደካማ ጐን የተሰጡትን አስተያየቶች በመገምገምና የማስተካከያ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ አገልግሎት አሰጣጣችን ወጥ ከማድረግና በጥራትና በቅልጥፍና ከመስጠት አንፃር የተሻሻሉ ሁኔታዎች መኖራቸው፤
- ተገልጋዮችን/ደንበኞችን/ በህጉ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ህጉን ተከትለው በተፈቀደላቸው ዓላማ ብቻ እንዲሰሩ የመከታተልና የመደገፍ ተግባራት መከናወኑ፤
- ወርሃዊ የዕቅድ አፈፃፀም ለፈፃሚ አካላት ቀርቦ እየተገመገመ ለሚመለከተዉ አካላት መድረሱ፡፡

### 1.7.2. ውስጣዊ ደካማ ጎኖች

- አመራሩ እራሱን አብቅቶ በስሩ ያሉ ሰራተኞችን የተነሳሽነትና የኔነት ስሜት እንዲኖራቸው ከማብቃት አንፃር የተሟላ አለመሆኑ፤
- ከዚህ በፊት የተዘጋጁ መመሪያዎችና ማንዋሎች ሙሉ በሙሉ በመፈተሽ አለመስተካከላቸውና ተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች አለመዘጋጀታቸው፤
- ከበላይ አመራሩ የሚሠጡትን አቅጣጫዎች በተሟላ መልኩ የማውረድና ግልፅነት ፈጥሮ ፈፃሚው እንዲፈፅም ያለማድረግ፤
- የተቀመጠውን ህግ ተረድቶ ወጥ የሆነ አገልግሎት መስጠት ላይ ክፍተት መኖሩ፤
- የሰራተኛውንና የአመራሩን የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት በመለየት የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት የሚያስችሉ ስልጠናዎች በዕቅድ መሰረት አለመሰጠታቸው፤
- ከፌዴራል ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ከክልሎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ፈጥሮ ተቀናጅቶና ተናበ ህዝባዊ ተልእኮን ከማስፈፀም አንጻር ክፍተት ያለ መሆኑ፤
- በህዝብ ግንኙነት ስራችን የኤጀንሲውን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ለደንበኞች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለህበረተሰቡ ማስተዋወቅ ላይ በተጠናከረና ተከታታይነት ባለው መልኩ አለመሰራቱ፤
- በህጉ መሰረት ጥሩ አፈፃፀም ያላቸውን በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በመለየት

የማበረታት ተግባር ለማከናወን የአቅም ውስንነት ያለ መሆኑ፣

- የተቋሙን የመረጃ ቋት በአዲስ መልክ በመገንበት አስፈላጊ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝ ላይ ክፍተት መኖሩ።

### 1.7.3. ዉጫዊ ሁኔታዎች

#### ሀ/ ምቹ ሁኔታዎች

- በሀገሪቱ ለስራ ምቹ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ስትራቴጅዎችና ህጎች መኖራቸዉ፤
- መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የልማት፣የዴሞክራስና ስርዓት ግንበታ አጋር አለካት መሆናቸዉን ፅኑ እምነት ያለዉ መሆኑ፤
- በአገራችን የተረጋጋ ፖለቲካና ሠላም መኖሩ፤
- የዜጎች የመደራጀት መብት ያረጋገጠ አዋጅ ቁጥር 621/2001 መዉጣቱ፤
- ሃገራችን መካከለኛ ገቢ ካላት አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተጀመረዉ ሁለገብ ጥረት አካል የሆነዉ 2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መዉጣቱና 1ኛ ዙር ዕቅድ አፈጻጸም መሰረት ጥሎ መለፉ፤

#### ለ/ ስጋቶች

- አንዳንድ የዉጭ |ይሎች አዋጁንና በደንቡን መሰረት አድረገዉ የወጡ መመሪያዎች የሚያጥላላ ዘመቻ በመክፈት በየአጋጣሚዎች ሁሉ ተፅዕኖ ለማሣደር የሚያደርጉት ሙከራ እንደቀጠለ መሆኑ፤
- ክልሎች የፌዴራል አዋጅ ቁጥር 621/2001 ጋር የሚጣጣም የራሳቸዉ የህግ ማዕቀፍ ባለመዉጣታቸዉ ተመጋጋቢ፣ የተቀናጀና ወጥ የሆነ ግንዛቤ ይዞ አለመፈፀም፤
- አንዳንድ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከተፈቀደላቸዊ ዓላማ ዉጭ የመስራት አመለካከትና ፍላጎት መኖሩ፤

### 1.8.የዕቅዱ አፈጻፀም አቅጣጫዎች፤

- አመራሩንና ሰራተኛውን በአመለካከት፣ በእውቀትና በክህሎት የሚያሳድጉ የሰው ኃይል ልማት ተግባራትን በማከናወን ይፈጸማል፤
- አመራሩንና ሠራተኛውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉበት፣ የጋራ እሴቶቻችን የሚሰርፁበት እና መልካም አስተዳደር የሚገነቡበት አሰራሮች በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ ይከናወናል፤
- የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥና የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በማድረግ ወጭ ቆጣቢ፣ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት በመስጠት ይፈጸማል፤

- ከዚህ በፊት የተዘጋጁ መመሪያዎችና ማንዋሎችን በመፈተሽ የማስተካከል በተጨማሪም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችና ማስቻያዎችን በማዘጋጀት ይፈጸማል፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱን ወቅታዊና ተከታታይነት ባለው መንገድ በማከናወን ገላጭ እና ትስስርነት ያለው የተሟላ መረጃ በመያዝ ሞዴል የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን በማበረታት የሚከናወን ይሆናል፤
- የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተጠናከረ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን በመስራት አዋጁን፣ ደንቡና መመሪያዎችን እንዲሁም የኤጀንሲውን በጐ ገጽታዎች ለህበረተሰቡ የሚያስተዋውቅ አቅጣጫን በመከተል ይፈጸማል፤
- ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመረጃ አያያዛችንን የተሟላ በማድረግ ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት በመስጠት ይፈጸማል፤
- ከክልልና ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር ያለንን የስራ ግንኙነት የጋራ ፎረሞችን በማጠናከር ለአዋጁ መተግበር ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ይከናወናል፤
- የተቋሙን የአገልግሎት ተደራሽነት በማስፋት የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት ይፈጸማል፣
- ልዩ ድጋፍና ትኩረት የሚሹ ዜጐችን ህገ መንግስታዊ መብቶቻቸውን ማስከበር፣ ተሳትፎቸውንና እኩል ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ይከናወናል፤
- የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ከፌዴራል ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ክክልሎች ጋር ቅንጅት በመፍጠር ይከናወናል፤

□□□ □□□

## 2. ቁልፍ ተግባር

የሰራተኛውንና የአመራሩን የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት አቅርቦት ማነቆዎችን ለይቶ በመፍታትና የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ እንደ ለውጥ ሠራዊት ሆኖ የሚፈፅም አመራርና ሰራተኞችን በመፍጠር እና የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባርን ቀጣይነት ባለው መልኩ ትግል ለማድረግ እንዲሁም ከህዝብ ክንፉና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት የኤጀንሲውን ተልዕኮ በማሳካት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቋሙ የቁልፍ ዕቅድ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

**ዓላማ1፡- የሠራተኛውና የአመራሩን የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ለይቶ በመፍታትና የተለያዩ አሰራሮችና አደረጃጀቶችን በመዘርጋትና የተጀመረውን ለውጥ በማስቀጠል ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊ፣ ወጪ ቆጣቢና ደንበኛ ተኮር አገልግሎት የሚሰጥ የለውጥ ሠራዊት በመገንባት የኤጀንሲውን ራዕይና ተልዕኮ ማሳካት፡፡**

**ግብ 1፡- የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓቱ ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስቀጠል ተቋማዊ ተልእኮን በተሟላ መልኩ ሊፈጽም የሚችል የለውጥ ቡድን አደረጃጀቶችን ማጠናከር፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የተቋሙን የ2008 በጀት አመት የውጤት ተኮር እቅድ በማዘጋጀት ቻርተር መፈራረም፣
- የውጤት ተኮር የምዘና ስርዓቱን ለማስቀጠል በጥራት፣ በጊዜና በመጠን በተሟላ መልኩ የተከናወኑ ተግባራት መለካታቸውን በየሳምንቱ በቅርበት በመከታተልና በመደገፍ ግብረ መልስ መስጠት፤
- በፈፃሚዎች መካከል የተቀራረበ የአመለካከትና የሙያ ክህሎት ለመፍጠር ዕለታዊና በዳይሬክቶሬት ደረጃ በየሳምንቱ የሚካሄዱ ግምገማዎችና የመማማሪያ መድረኮች ጊዜቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የዳይሬክቶሬቶች፣ የስራ ቡድኖችና ፈፃሚዎችን ሳምንታዊ ዕቅድና ሪፖርቶችን በመገምገምና ስራን መሰረት ያደረገ ውጤት በማስቀመጥ ግንባር ቀደሞችን በመለየት ዕውቅና መስጠት፤
- የግንባር ቀደም የዳይሬክቶሬቶች መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር በየሩብ አመቱ ልምድ ልውውጥ ማድረግ፤
- የተቀመጡትን የጥራት፣ የጊዜና የመጠን መለኪያ ስታንዳርዶች በመፈተሽ በየጊዜው በማሻሻል ለሰራተኛው ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
- ዳይሬክቶሬቶችና ቡድኖች እንደየ አደረጃጀታቸው የተሰጣቸውን ተልዕኮ ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲወጡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

- የበላይ አመራሩ ከፈፃሚ ሰራተኞች ጋር በየወሩና በየሩብ አመቱ አጠቃላይ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ተቋማዊ ድጋፍ ማድረግ፤

**ግብ 2፡- የሠራተኛውንና የአመራሩን የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት በመለየት አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት የመፈፀም አቅማቸውን ማጎልበት።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የአመራርና የሠራተኞችን የአመለካከት፣ የእውቀት፣ የክሕሎትና የግብአት ማነቆዎችን እና የአፈፃፀም ክፍተቶችን በመለየት የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- አዲስ ለሚቀጠሩ ሰራተኞች በአዋጁ፣ በደንቡ፣ በመመሪያዎችና በዉጤት ተኮር ስራ ምዘና ስርዓት ላይ ስልጠና በመስጠት ወደ ስራ ማስገባት፤
- ለከፍተኛና መካከለኛ አመራር የተሽከርካሪ መንጃ ፍቃድ ስልጠና
- ለሹፌሮች የቴክኒክ ስልጠና መስጠት፤
- ለሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች የሚሰጡ ስልጠናዎች
  - ለሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች በለውጥ ሰራዊት ግንባታና በመልካም አስተዳደር ማንዋል በውጤት ተኮር ስርዓት ምዘና አፈፃፀም እና የመረጃ አያያዝ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
  - በስነ ምግባር መርሆዎች፣ የሞያ ስነምግባር፣ በሙስና ወንጀል፣ የደረቅ ወንጀል ልዩነቶች፣ ስለ ተሻሻለው የፀረ ሙስና አዋጅ፣ በኤጀንሲው የስነ ምግባር ደንብ እና በፀረ ኪራይ ሰብሳቢነትና በመልካም አስተዳዳር ጉዳዮች ዙሪያ፤
  - በመረጃ ነፃነት ዙሪያ ስልጠና መስጠት፤
  - በሴኩላሪዝም፣በልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስትና የፌደራል ሥርዓት ምንነትና አቅጣጫና የሲቪል ሰርቪስ ሚና ስልጠና መስጠት፤
  - በአገርቱ ፖሊስና እስትራቴጅ ዙርያ፤
  - ፀረ ኪራይ ሰብሳቢነትና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች፤
  - በፋይናንሻል ኦዲት፣ በግዥ ኦዲት እና በንብረት ኦዲት፤
  - በመረጃ አያያዝ፤
  - ለሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች በደንበኞች አገልግሎት፣ በሰዉ ሃይል አመራርና ሲቪል ሰርቪስ መመሪያዎች ላይ ስልጠና መስጠት፤
- ለተቋሙ መዝገብና ማህደር ሰራተኞች
  - በሪከርድ አያያዝ (Record management) ስልጠና መስጠት
- ለዋና ዳይሬክቶሬት ኦፊሰሮች እና ለሌሎች ስራው ለሚመለከታቸው ኦፊሰሮች
  - በፕሮጀክት ሳይክል ማናጅመንት፤
  - በፋይንሽያል ኦዲት እና ኮምፒልያንስ ኦዲቲንግ፤
  - በንብረት ማጣራት፣ ማስተላለፍና ማስወገድ ላይ ስልጠና መስጠት
- ኮሙንኬሽን ባለሙያዎች
  - በእንግልዘኛ ቋንቋ
  - በዳታ ቤዝ ማናጅመንት
  - ፎቶና ድምጽ ኢድቲንግ

- በአርቲክል ዝግጅት
- በማህበራዊ ድረገጽ አጠቃቀም ስልጠና መስጠት

**ግብ 3. በለውጥ ሰራዊት መልክ አገልግሎትን በመስጠት የተገልጋዮች እርካታ 100% ማረጋገጥ።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የሰው ኃይሉን ህጉን ጠንቅቆ አውቆ እንዲፈጽም በማብቃት ለደንበኞች ወጥ እና ጥራት ያለዉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በተቋሙ ሁሉም የስራ ክፍሎች ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት አገልግሎት አሰጣጣችን ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ መጠይቆችን በማዘጋጀት፣የሀሳብ መስጫ ሳጥንና መዝገብ በማዘጋጀት አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ በደካማ ጐን የተሰጡ አስተያየቶችን ለሚመለከተዉ የስራ ክፍሎች በማቅረብ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥና ለውጡን መከታተል፤
- በየእለቱ ደንበኞች የሚያቀርቡትን የመረጃ ጥያቄዎች በጥራትና በፍጥነት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ከተገልጋዮች ጋር በሚደረጉ የምክክር መድረኮችና ስልጠናዎች የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ እንደ አንድ አጀንዳ በመያዝ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ክፍተቶቹን ማስተካከል፤
- የዉስጥና የዉጭ ተገልጋዮች የሚያቀርቡትን ቅሬታዎች መለየትና ተቀብሎ በማጣራት ማስተካከያ ማድረግ፤
- አዲስ የአገልግሎት መስጫ ቅ/ጽ/ቤት ለመክፈት የሚያስችል ልምድ ከሌሎች መስሪያቤቶች መዉሰድና የአጠቃላይ ጥናት ማድረግ፤
- የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት በየ 6 ወሩ በማድረግ ውጤቱን ለስራ ግብዓትነት መጠቀም፤

***ግብ 4፡- የጥቆማ አቀራረብና የቅሬታ አፈታት ሂደትን በማሻሻል ፈጣን ምላሽ መስጠት።***

**ዝርዝር ተግባራት**

- የቀረቡ ጥቆማዎችን መሠረት በማድረግ የማጣራት ሥራ መስራት፤
- በጥቆማ መጣራት ሂደት መራጃዎችን አደራጅቶ መያዝ፣
- የታዩ ግድፈቶችን እንዲስተካከሉ ማሣወቅ/እርምጃ/ መውሰድ እና በውሣኔው መሠረት ስለመፈፀሙ ማረጋገጥ።
- ከስራ ክፍሎች አቅም በላይ የሆኑትን በበላይ አመራሩና በማናጅመንት ካዉንስል አቅርቦ ማስወሰን

**ግብ 5፡- ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ትግሉን ማጠናከር፤**

ዝርዝር ተግባራት

- ጠንካራ ቁመና እና የተቀራረበ አፈፃፀም ያለዉ የለዉጥ ሰራዊት በመገንባት ንቅናቄ መፍጠር፤

- የሥነ-ምግባር እሴቶችን በማስረጽ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባርን መታገል፤
- ለሙስና ተጋላጭነት ያላቸውን ተግባራት የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ክፍተቶቹን፤ በአሰራር በመዝጋት ክትትል ማድረግ፡-

| የሙሰና ምንጭ | መታገያ ስልቶች |
|---|---|
| *የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አዲስ ምዝገባ እና የዕድሳት ፈቃድ መስጠት፤* | • *በቡድን ተደራጅቶ በማከናወን፤*<br>• *በየቀኑ በሚደረጉ የውሎ ግምገማ*<br>• *ፈቃዱ በህጉ መሰረት የተሰጠ መሆኑን ዳይሬክቶሬቱ በሚያደርገው ክትትል፣*<br>• *በተዘረጋው የቅሬታ ማቅረቢያ ስርአት መሰረት ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በማጣራት*<br>• *ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስነ ምግባር መመሪያ መሰረት ክትትል በማድረግና በመታገል፤* |
| *ለበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ልዩ ልዩ የድጋፍ አገልግሎቶች ሲሰጥ ማለትም፡-*<br>• *የገቢ ማስገኛ የሥራ ፈቃድ*<br>• *ከቀረጥ ነፃ የድጋፍ ደብዳቤ*<br>• *ህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ መስጠት*<br>• ለዉጭ አገር ዜጎች የስራ ፍቃድ ስሰጥ | • *በቡድን ተደራጅቶ በማከናወን*<br>• *በየቀኑ በሚደረጉ የውሎ ግምገማ*<br>• *ከደንበኞች የሚቀርቡ ጥቆማዎችን ተቀብሎ በመገምገምና በማጣራት*<br>• *ህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ እና ከቀረጥ ነፃ ዳይሬክቶሬቱ አረጋግጦ እንዲፈረም በማድረግ*<br>• *የገቢ ማስገኛ የስራ ፈቃድ* በበላይ አመራሩ *ፊርማ በማፅደቅ፤*<br>• *በህግና በመመሪያ መሰረት የድጋፍ ደብዳቤው እና ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን ዳይሬክቶሬቱ በመከታተልና ከህግ አግባብ ውጪ ከሆነ የእርምት ማስተካከያ በመስጠት፣*<br>• *ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስነ ምግባር መመሪያ መሰረት ክትትል በማድረግና በመታገል*<br>በአገልግሎት አሰጣጥ ወጥ የሆነ መስፈርት በማስቀመጥ በህጉ፤ ደንብና መመሪያ ተከትሎ እንዲፈፀም ማድረግ፤ |
| *የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን በዴስክ ክትትልና በመስክ ክትትል ወቅት በተገኙ የአሰራርና የህግ ጥሰት ግኝቶች ላይ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች አለመውሰድ* | • *ተግባራትን በቡድን በማከናወን*<br>• *በዴስክ ክትትል በተገኙ ግኝቶች በህግ አግባብ የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ዳይሬክቶሬቱ በመከታተል፣*<br>• *በዴስክ ክትትል በተገኙ ግኝቶች እና የመስክ ክትትል ሪፖርቶችን ዳይሬክቶሬቱ በመመርመር መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች በህግ አግባብ የተወሰዱ መሆኑና በማረጋገጥና ክፍተት ካለው እንዲስተካከሉ በማድረግ፣*<br>• *በተዘረጋው የቅሬታና የጥቆማ ማስተናገጃ መሰረት ከደንበኞች በሚቀርቡ ጥቆማዎችን በማኔጅመንት እየታዩ በሚሠጠዉ አቅጣጫ መሰረት በማጣራት፣*<br>• *ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስነ ምግባር መመሪያ መሰረት ክትትል በማድረና በመታገል* |
| *ባለሙያዎች ከደንበኛ ጋር አላስፈላጊ ግንኙነት ሲታይባቸው ፤* | • *የሚቀረቡ ጥቆማዎችን በማጣራት*<br>• *በየቀኑ በሚደረጉ የውሎ ግምገማ ላይ የርስ በርስ ትግል በማድረግ*<br>• *ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስነ ምግባር መመሪያ መሰረት ክትትል በማድረግና በመታገል* |

| | |
|---|---|
| *በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በተለያየ ምክንያት ሲዘጉ ንብረታቸውን አጣርቶ ማስተላለፍ እና በስራ ላይ ያሉ ድርጅቶች ንብረት እንዲወገድላቸው ሲጠይቁ ንብረት የማስወገድ ተግባር ሲከናወን ማለትም*<br>• *ንብረት ቆጠራ ላይ*<br>• *ማስተላለፍ ላይ*<br>• *ንብረቱ በሽያጭ በሚወገድበት ወቅት፣* | • *በየቀኑ በሚደረጉ የቀን ውሎ ግምገማ*<br>• *ንብረት የማጣራት የማስተላለፍና ማስወገድ ሲከናወን ሦስት ባለሙያዎች በአንድ ላይ በቡድን በማከናወን የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣*<br>• *ከመተላለፉ በፊት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ አመራሩ አቅርቦ በማፀደቅ፣*<br>• *በተዘረጋው የቅሬታና የጥቆማ ማስተናገጃ ስርአት ከደንበኞች በሚቀርቡ ጥቆማዎችን በተቀመጠዉ አቅጣጫ በማጣራትና በመተግበር፣*<br>• *በተዘጋጀው የንብረት ማስተላለፍና ማስወገድ ቼክ ሊስት መሰረት ንብረቱ ተቆጥሮ የተላለፈ መሆኑን ዳይሬክቶሬቱ ክትትል አድርጐ በማጣራት አላግባብ ከሆነ የማስተካከያ እርምት በመውሰድ፤*<br>• ህጉ፣ደንቡና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፤<br>• በፐርፎርማንስ ኦዲት የተሰጡ ግብአቶችን መፈፀም፣ |
| • *ወጥ የሆነ አገልግሎት አለመስጠትና የደንበኞች አላግባብ ማመላለስ፤* | • *በየቀኑ በሚደረጉ የቀን ውሎ ግምገማ ላይ በመተጋገል፣*<br>• *ስራዎችን* በመደ*ጋገፍና በጋራ በመስራት*<br>• *በተዘረጋው የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት መሰረት ደንበኞች የሚያቀርቡትን ቅሬታና ጥቆማዎችን* በወጣዉ *መመሪያናአቅጣጫ መሰረት በማጣራትና በማስተካከል፣*<br>• *ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስነ ምግባር መመሪያ መሰረት ክትትል በማድረግና በመታገል*<br>• በዜጎች ቻርተር የተቀመጠዉን ስተንደርድ በመተግበር |
| • *የሙያ ሥነ-ምግባር መጓደል፣*<br>• *ውስብስብና አሰልቺ ቢሮክራሲ አልፎ አልፎ መከሰት፣*<br>• *በሰራተኞች መካከል የሚፈጠር የግልፀኝነት መጉደል፣* | • *በስነ- ምግባር መመሪያ ላይ በየጊዜው ስልጠናዎችን በመስጠት ፈፃሚዎች የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ ማድረግ፤*<br>• *የተዘጋጀዉን የሥነ- ምግባር ደንብ ስራ ላይ በመዋል፤*<br>• ባለጉዳይ ለአላስፈላጊ እንግልት ሲዳረግ ዳይርክቶሬቱ ተከታትሎ የችግሩን ምንጭ በማጥራት የማስተካከያ እርምጃዎች በወሰዳሉ፤<br>• የሃብት ማሳወቅና የምዝገባ አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ፣<br>• የጥቆማና የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአት መሰረት ጥቆማዎችን ተቀብሎ በማጣራት በህግ አግባብ እርምት በመውሰድ፣<br>• በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከተገልጋዮች መረጃ ማሰባሰብ፣<br>• የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን በማጎልበት፣ |
| • *ነዳጅ አጠቃቀም*<br>• *የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ በምፈጸምበት ጊዜ* | • *በተቋሙ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በሊትር የሚሄዱትን ኪሎ ሜትር በማስለካት፣*<br>• *በተለካው መሰረት የነዳጅ አጠቃቀማቸውን ለማወቅ መኪኖች በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የኪሎሜትር ምዝገባ በማካሄድ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ፤*<br>• መኪኖች ለሥራ የተጠቀመዉ ክፍል የተጓዘበትን ቦታ እንዲያረጋግጥ በማድረግ፤<br>• ነዳጅ በተመደበዉ ሰራተኛ እንዲሞላ በማድረግ *የተሽከርካሪ ተጠቃሚ ሰራተኞች በነዳጅ አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር እንዲያደርጉ መዲደግ፡፡*<br>• *በግዥ መመሪያ መሰረት የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ በመፈፀም፡፡*<br>• በፐርፎርማንስ ኦዲት የተሰጡ ግብአቶችን በመፈፀም፣ |

**ግብ 6፡- የህዝብ ክንፍ አደረጃጀትን በመጠቀም ተቋማዊ ተልዕኮን በለውጥ ሰራዊት መልክ መፈፀም፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የሕዝብ ክንፉን ማደራጀት፣ ማጠናከርና የተልእኮ ግልጸኝነት በመፍጠር እንደ አደረጃጀቱና የአላማ ስምሪቱ በመለየት ተልዕኮ መስጠት፤
- ከህዝብ ክንፍ ጋር ቋሚ የሆነ የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ በኤጀንሲው እቅድና አፈጻጸም፣ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ እና በአዋጁ፣ በደንቡና በስነ ምግባር ህግ ዙሪያ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣
- የህዝብ ክንፉን መልካም ተሞክሮዎች በመቀመር ማስፋፋት፤
- የብዙሃን ማኅበራት ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው በመደራጀት በሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲኖር አብሮ መስራት፤

## 2.2. አበይት ተግባራት

### 2.2.1. ምዝገባ፣ ፈቃድና እድሳት እንዲሁም በህጉ የተቀመጡ ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት

**ዓላማ፡-** በአዋጁ፣በደንቡና፣ በመመሪያዎቹ መሠረት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን በመመዝገብ፣ ፍቃድ በመስጠትና ፍቃዳቸውን በማደስ እንዲስፋፉና እንዲበረታቱ በማድረግ አገራችን የነደፈችውን የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የበኩላቸውን ድጋፍና የማሳለጥ ሚና እንዲወጡ ማድረግ፣

**ግብ1፡- የምዝገባ መስፈርቱን አሟልተው ለሚመጡ አዳዲስ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን 100% መመዝገብና ፍቃድ መስጠት፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ለመመዝገብ ወደ ኤጀንሲው ከመምጣታቸው በፊት ባሉበት ቦታ ሁነው ወይም ከመጡ በኂላ የቅድመ ምዝገባ መረጃ መስጠት፤
- አዲስ የሚመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የምሥረታ ሠነዶቻቸውን በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተረጋግጦ የመጣ መሆኑን አረጋግጦ የምዝገባ አገልግሎት መስጠት፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለምዝገባ ያመጡት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል የአንድ ሴክተር ከሆነ በሴክተር መሥሪያ ቤቱ እንዲገመገም መላክ፤
- ዘርፈ ብዙ የሆኑ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በኤጀንሲው ባለሙያዎች መገምገም፤

- ለመመዝገብ የመጡት የኢትዮጵያ ነዋሪዎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት እንዲሁም የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሆኑ በተፈቀደላቸው ልማታዊ ዓላማዎች ብቻ መወሰናቸዉ ማረጋገጥ፤
- የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ለምዝገባ ሲመጡ ሠነዳቸው የተሟላና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተረጋግጦ የመጣ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ለምዝገባ የመጡት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ከሆኑ ሌሎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢ ምንጫቸው ከ90% ያላነሰ ከሀገር ውስጥ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ለመመዝገብ የሚመጡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን በአዋጁና በደንቡ መሰረት ማሟላት ያለባቸውን መረጃዎችና ሰነዶች ማቅረባቸውን በማረጋገጥ መመዝገብና ፈቃድ መስጠት፣
- የምዝገባ መስፈርቶችን አሟልተው ላልቀረቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በህጉ መሠረት የክልከላ ደብዳቤ መስጠት፡፡

**ግብ 2፡- በ2008 ዕድሳት ለሚደረግላቸው 1478 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በህጉና በደንቡ መሠረት የእድሳት አገልግሎት መስጠት፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ዕድሳት ከመደረጉ በፊት ፋይሎችን መመርመርና መረጃ መያዝ፤
- በበጀት ዓመቱ ፈቃዳቸውን የሚያሳድሱ 1478 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለእድሳት የሚያበቁ መስፈርቶችን /ሰነዶችን/ መሟላታቸውን በማረጋገጥ የእድሳት ፈቃድ መስጠት፤
- ሦስት ዓመት የስራ ክንዉን ሪፖርት ማቅረባቸውንና 70/30 ጠብቀዉ መስራታቸዉን በዴስክ ኦዲት መረጋገጡን በማየት የእድሳት ፈቃድ መስጠት፤
- አዲስ ለተመዘገቡትም ሆነ ነባር በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት
- በተለያየ ምክንያት በስራ ላይ እያሉ ፍቃዳቸዉን ሳያሳድሱ የቀሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በመለየት ዉሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ልዩ ልዩ ተብለዉ የተመዘገቡና በኤጀንሲዉ አዋጅ የማይሸፈኑ እና እስከ 2007 በጀት ዓመት የአደረጃጀት ማስተካከያ ያላደረጉትን እንዲዘጉ ማድረግ፡፡

## 2.2.2 የዴስክና የመስክ የክትትልና ድጋፍ ሥራ

ዓላማ፡-የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በአዋጁ፣ በደንቡና፣ በመመሪያዎቹ መሠረት እየሰሩ መሆናቸውን የዴስክና የመስክ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አገራችን የነደፈችውን የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዉስጥ የበኩላቸውን ድጋፍና የማሳለጥ ሚና እንዲወጡ በማድረግ የህዝቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

**ግብ1፡- 3000 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በአዋጁ፣ ደንቡና መመሪያዎች መሠረት መስራታቸውን ለማረጋገጥ ፋይላቸውን የዴስክ ክትትል በማድረግ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሣደግ፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- 3000 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ፋይል ጥቅል የዴስክ ክትትል በማድረግ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሣደግ፡፡
  - በኢትዮጵያ በጀት አመት የሚጠቀሙ ድርጅቶችና ማህበራት የ2007 ዓመት የአፈፃፀምና የኦዲት ሪፖርት እንዲሁም የ2008 እቅድ በመመርመር ግብረ መልስ መስጠት፤
  - የበጀት ዘመናቸው በአውሮፓ የሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት የ2015 የአፈፃፀም ሪፖርት፣ የኦዲት ሪፖርት፣ የቋሚ ንብረት ዝርዝርና የ2016 የሥራ ዕቅድ ማቅረባቸውንና በህጉ መሠረት መፈፀማቸውን ማረጋገጥና ግብረ መልስ መስጠት፤
  - የፕሮጀክት ስምምነቶችን ህጉ ጠብቀው የተደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
  - በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተቀጣሪ የሆኑ ሰራተኞች የገቢ ግብር እየከፈሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
  - በ2007 ዓ.ም ዴስክ ክትትል የተደረገባቸው ድርጅቶች የተያዘው መረጃ መነሻ በማድረግ የነበሩ ግድፈቶች መስተካከላቸው ማረጋገጥ፤
  - በ4 አመት ውስጥ የህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ እና የገቢ ማስገኛ ፈቃድ የተሰጣቸ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ለይቶ መረጃ በመያዝ አፈፃፀማቸው በህጉ መሰረት መሆኑን በመከታተልና በማረጋገጥ፤
  - የ70/30 እና 90/10 በአዋጁ፣ በደንቡናና በመመሪያው መሰረት የፈፀሙ መሆኑን መከታተልና በህጉ የፈፀሙትን ማበረታታት እና ህጉን ያልጠበቁ ላይ እርምት መዉሰድ፤
  - በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በዴስክ ክትትል ወቅት የተገኙ ጉድለቶቻቸው እንዲያስተካክሉ ግብረ መልስ መስጠት በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ወደመስመር የገቡ መሆኑን በመከታተል መረጃ መያዝ፤
  - በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በራሳቸው የመዘጋት ጥያቄ ሲያቀርቡ በማጣራት መዝጋት፣
  - በህግ አግባብ ባለመስራታቸው የሚዘጉ ድርጅቶችን በማጣራት መዝጋት፡፡
  - በወንጀል መጠየቅ ያለባቸው ሰዎች እና ድርጅቶች ለህግ እንዲቀርቡ ማድረግ፡፡
  - የላቀ አፈፃፀም ያላቸዉን በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መስፈርት በማዘጋጀትና በመለየት የማበረታታት ተግባር በማከናወን ጥሩ የፉክክር መንፈስ መፍጠር፤
- የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ለልማት ያዋሉትን በጀት/Capital/ ምን ያህል እንደሆነ መረጃውን ለይቶ መያዝ፡፡

- የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አጠቃላይ ያሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ ጥራት ያለው መረጃ አደራጅቶ መያዝ፤

**ግብ2፡- 1000 የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የመስክ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአዋጁ፣ በደንቡና በመመሪያዎች መሠረት በተቋቋሙት ዓላማ መሰረት መስራታቸውን በማረጋገጥ ዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ለክትትል ስራ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ለመስክ ሥራው ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸት፤
- በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ባስቀመጡት ዓላማና በህጉ መሠረት እየሰሩ መሆኑ ተጠቃሚ ዜጎችና በአካባቢው የሚመለከታቸውን ሴክተር መሥሪያቤቶች በማወያየት እንዲሁም በአካል ሥራውን በማየት ማረጋገጥ፤
- ድርጅቶችና ማኅበራት በመተዳደርያ ደንባቸው መሠረት እየሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ገቢ ማስገኛ ወይም ህዝባዊ መዋጮ እየሰሩ ከሆነ ከኤጀንሲው የተፈቀደላቸው መሆኑ እና በህጉ መሠረት ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፤
- የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ለመከላከል እንዲቻል አሰራራቸው መፈተሽና ማስተካከያ እንዲያደርጉ ድጋፍ ማድረግ፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አደረጃጀቶች እና ውጤታማነታቸው በትክክለኛ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ወጥ የሆነ የሪፖርት ፎርማት በማዘጋጀት መረጃ መያዝ፤
- ሃይማኖትና ልማት፣ ልማትና መብት ወዘተ እያቀላቀሉ ባልተፈቀደላቸው የሚሠሩ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን በመለየት እንዲያስተካክሉ ማድግ፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት የፆታ እኩልነት የተቀበሉና በተለይ ሴቶችን የማገዝ ልዩ ትኩረት ማድረጋቸው ማረጋገጥ፤
- የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ለልማት ያዋሉትን በጀት/Capita/ ምን ያህል እንደሆነ መረጃውን ለይቶ መያዝ፡፡
- በተገኙ ግኝቶች ልክ ተመጣጣኝ እርምጃ መወሰድና ውጤቱን መከታተል፡፡
- በዴስክ ክትትል ጥሩ አፈፃፀም ያላቸውን ድርጅቶች በመለየትና በመስክ ክትትል አፈፃፀማቸውን በማረጋገጥ ማበረታታት፡፡

## 2.2.3 የንብረት ማጣራት፣ ማስተላለፍና የማስወገድ ተግባር

**ዓላማ፡-** በክትትል ሥራ በህግ አግባብ ባለመስራታቸው፣ በራሣቸው ውሳኔና ፍቃዳቸውን ባለማሳደሳቸው የፈረሱ ድርጅቶችና ማህበራት ንብረት እንዲሁም በሥራ ላይ እያሉ ንብረት እንዲወገድላቸው

የሚጠይቁ ድርጅቶችን ንብረት አጣርቶ በማስተላለፍና በማስወገድ የህዝብ ሀብትና ንብረት አላግባብ እንዳይባክን ማድረግ።

**ግብ 1፡- በክትትል ስራ በሕግ አግባብ ባለመስራታቸው የመዘጋት ውሣኔ የተወሰነባቸው እና በራሳቸው ጥያቄ የሚዘጉ 100% እንዲሁም ከዚህ በፊት ተዘግተው የማጣራት፣ የማስወገድና ማስተላለፍ ስራ ያልተጠናቀቁ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ሀብትና ዕዳቸውን በማጣራት ቀሪ ንብረታቸውን ተመሳሳይ ዓላማ ወይም ተቀራራቢ ወይም ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ላላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ማስተላለፍ።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የመዘጋት ውሳኔ የተወሰነባቸው ድርጅቶችና ማኅበራት መለየት ጥራት ያለው መረጃ መያዝ፤
- የበጎ አድራጎቶችና ማህበራት ንብረት ማሸግ፤
- የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ሂሳብ እንዲዘጋና እንዲመረመር ማድረግ፤
- ንብረት ቆጠራ በማድረግ ሀብትና ዕዳ መለየት፤
- ንብረቶቹን እንደየአይነታቸው መለየትና ማደራጀት እንዲሁም ባለቤትነትን ማረጋገጥ፤
- የሚሸጡ፣ የሚተላለፉ፣ የሚቃጠሉና የሚቀበሩ ንብረቶችን መለየት፤
- ንብረቶችንና የሂሳብ ሰነዶችን በአመች ቦታ ሰብስቦ ማቆየት፤
- የገበያ ጥናት ማድረግ የሚሸጡ ንብረቶችን ግምት በማውጣት የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀትና ማጫረትና መሸጥ፤
- ባለመብቶችን በጋዜጣ በመጥራትና በመለየት ለባለመብቶቹ እዳ መክፈል፤
- የሚተላለፉ ገንዘብና ንብረቶች በውስጥ ማስታወቂያ ይፋ ማድረግ፤
- ገንዘብና ንብረት እንዲተላለፍላቸው የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መቀበልና በመመዘኛ መሰረት በማጣራ ገንዘብና ንብረት መተላለፍ የሚገባቸውን ድርጅቶች መለየት፤
- ንብረት ወይም ገንዘብ እንዲተላለፍላቸው የተመረጡ ድርጅቶችን ለበላይ አመራር አቀርቦ በማስወሰን በውሳኔው መሰረት ገንዘብ ወይም ንብረት ማስተላለፍ፤
- የተላለፈውን ንብረት ወይም ገንዘብ በሰነድ ማስፈር ሪፖርት ማዘጋጀትና ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍና መያዝ

**ግብ 2፡- በስራ ላይ እያሉ ንብረት እንዲነሳላቸዉ ወይም እንዲወገድላቸው ከዚህ በፊት የጠየቁትን 100% በበጀት ዓመቱ የሚጠይቁ 50% የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ንብረት ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በመመሪያዉ መሰረት ማስወገድ ወይም ማስተላለፍ።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የንብረት ይወገድልኝ ጥያቄ የቀረበባቸው ንብረቶች እንደየ አይነታቸው በመለየትና በማደራጀት ባለቤትነትን ማረጋገጥ፣
- የሚተላለፉና የሚወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር መረጃ በመያዝ የሚተላለፉ ንብረቶችን በውስጥ ማስታወቂያ ይፋ ማድረግ፣
- ንብረት የሚተላለፍላቸውን በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን በመለየት ለበላይ አካል አቅርቦ በማስወሰን ንብረት ማስተላለፍ፣
- የሚወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር መረጃና ሠነድ በማዘጋጀት መሸጥ ያለባቸውን ንብረቶች ለብቻ መለየት፤
- የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ተጫራቶችን ማጫረት፤
- የጨረታ ውጤት ማዘጋጀትና ይፋ በማድረግና የውሳኔ አስተያየት ለበላይ አካል በማቅረብ በማስወሰን መሸጥ፤
- በሌላ/በመቅበርና በማቃጠል/ መወገድ ያለባቸውን ንብረቶች በመለየት በመመሪያው መሰረት ማስወገድ፤

## 2.2.4. የሕግ አገልግሎት መስጠት

**ዓላማ፡- የሕግ አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል የሕግ ጥሰት ፈጽመው የተገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በወንጀልና በፍትሐብሔር እንዲጠየቁ በማድረግ እንዲሁም አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያዎቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር።**

**ግብ 1፡- ወንጀል ፈጽመዉ የተገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም የስራ መሪዎች በመለየት መረጃን በማሰባሰብ እንዲከሰሱ ማድረግ።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- በተፈጸሙ የህግ ጥሰቶች የህግ ተጠያቂነትን በሚገባ በመለየት መረጃዎችን አሰባስቦ በማደራጀት ክስ እንዲመሰረት ማድረግና ተፈፃሚነቱን መከታተል፤
- የተዘጉ ድርጅቶች ሠራተኞች በሚያቀርቡት የፍትሐብሔር ክሶች ጣልቃ በመግባት መልስ በማቅረብና በመከራከር ተገቢው ፍትህ እንዲሰጥ ማድረግና ያለአግባብ በግለሰቦች እጅ የሚውሉ ንብረቶችንና ገንዘብን በህግ እንዲመለስ በማድረግ የህዝብ ሃብት እንዳይባክን መከላከል፤
- ከፍርድቤት ለሚቀርቡ ጉዳዮች በመረጃ የተደገፈ ግልጽ ምላሾችን በወቅቱ አዘጋጅቶ በመላክ በመረጃ እጥረት የሚከሰቱ ክፍተቶችን መሸፈን፤

**ግብ 2፡- አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስችሉ 2 መመሪያዎችና የአስራር ማንዋሎችን በማዘጋጀት አዋጁ ተግባራዊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀት እና ሌሎች አዳዲስ አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስችሉ መመሪያዎችና የአሰራር ማኑዋሎች የሚያስፈልጋቸው ተግባራት ካሉ በመለየት ማዘጋጀት፣
- በተለዩት መመሪያዎችና የአስራር ማኑዋሎች በማዘጋጀት ከውስጥና ከውጪ ደንበኞች አስተያየቶች በመቀበልና እንደግብዓት ማካተት፤
- ሥራ ላይ የዋሉ የአሠራር ማንዋሎችና መመሪያዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመፈተሽ መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች መረጃ በመያዝ እንዲስተካከሉ ማድረግ።
- ከባለድርሻ አካላትና በተለያዩ የምክክር መድረኮች ላይ በመገኘት የአዋጁን ዓላማ ማስረዳት፣

## ግብ 3.ለሚያቀርቡት የህግ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ለውስጥና ለውጪ ደንበኞች መስጠት።

- የተቋሙ ፈፃሚች በአዋጁና መመሪያዎች ላይ ግልፅነት እንዲኖራቸዉ ማድረግ፤
- እያንዳንዱ ህግ በሌላዉ ህግ አፈፃፀም ላይ የሚኖረዉን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽኖዎችን በመለየት ሙያዊ የህግ ምክር አገልግሎት መስጠት፤
- በተቋሙ አመራር የህግ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የሚላኩ ፋይሎችን በማጣራት በህጉ መሰረት አስተያየት መስጠት፤

## 2.2.5. የኮሙኒኬሽን ሥርዓትን ማጠናከር

**ዓላማ፡- በመረጃ የበለፀገ ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች በመፍጠር እና በቅንጅት አብሮ በመስራት የተቋሙን ተልዕኮዎች ማሳካት፣**

**ግብ1፡- በዓመቱ 2 መጽሔት፣ 4 ብሮሸር፣ 12 ዜና ኤጀንሲና የተቋሙን መረጃ የያዘ 1 አጀንዳ፣20 ባነር እና 1ሰነድ በመረጃ ነፃነት ህግ መሰረት በማዘጋጀትና በማሳተም እንዲሁም በተለያዩ ዘዴዎች መረጃን ለውስጥና ለውጭ ደንበኞች ማሰራጨት።**

**ዝርዝር ተግባራት**

- መጽሔት፣ብሮሸር፣ ዜና ኤጀንሲ፣ባነር አጀንዳ፣ መመሪያዎች፣ ደንብና አዋጁን አሳትሞ መረጃዎችን ለደንበኞችና ለባለድርሻ አካላት ማሰራጨት፣
- የተዘጋጁትን መጽሄት፣ብሮሸር፣ዜና ኤጀንሲ፣መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችንና ቅጻቅጾችን በዌብ ሳይት ላይ በመጫን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ፣
- በኤጀንሲው የታተሙትን አዋጅ፣ደንብና መመሪያዎችና የተገልጋዩ ማንዋል ለደንበኞችና ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ማድረግ፣
- ኤጀንሲው ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት እና ለምዝገባ የሚያበቁ መስፈርቶችን በመረጃ ዴስክ በኩል ተደራሽ ማድረግ፣

- የተለያዩ ሚያዎችን የአየር ሰአት እና የህትመት አመዶችን በመግዛት የተቋሙን ተልኮ ማስተዋዋቅ፣
- በመገናኛ ብዙሃንና በመረጃ ነፃነት ህግ መሰረት ዜጎች የሚፈለጉትን የተቋሙን መረጃ በመለየት አሳትሞ ጥያቄው ሲቀርብ መስጠት፣
- የተሰራጨትን መረጃዎች በሙሉ ያስገኙትን የግንዛቤ ለውጥ ግብረ መልስ በመሰብሰብ መገምገምና ለቀጣይ ሥራ መዘጋጀት፣

**ግብ 2፡- በተቋሙ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሁነቶች በመፍጠር የሚዲያ ሽፋን እንደያገኙ በማድረግ ተገልጋዮች፣ዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ክልሎችና ህብረተሰቡ ተክክለኛ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ብሄራዊና አለም አቀፍዊ በዓላት ሲከበሩ የተለያዩ መልዕክቶችን ቀርፆ ለሚዲያ በመላክ እንዲተላለፍ ማድረግ፤
- የተቋሙ ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ ማዘጋጀት፤
- ከተቋሙ የህዝብ ክንፍ ጋር የሚደረጉ መደበኛ  የውይይት መድረኮች የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በኤጀንሲዉ እርምጃ የተወሰደባቸዉን ድርጅቶችና ማህበራት በሚዲያ ለሚመለከታቸዉ አካላት ትክክለኛ መረጃ መስጠት፤

**ግብ 3. የሚዲያዎች ሞኒተሪንግ እና ትንተና ስራ በማስራት ስለተቋሙ የሚቀርቡ አሉታዊና አዎንታዊ ዘገባዎች በመገምገም በአሉታዊ ዘገባዎች ላይ እርምት እንዲደረግባቸዉ በማድረግ ደንበኞች፣ ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰቡ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ፤**

- ለሞኒተሪንግና ትንተና የሚያስፈልጉትን የህትመት ሚዲያዎችን በኮንትራት እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- ማህበራዊ ሚዲያዎችን በስፋት በመከታተል ግብረመልስ መስጠት፤
- የተቋሙ ድረ-ገፅ ደረጃን በማሳደግ ጥቅም ላይ ማዋል፤
- የተለያዩ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን የሞኒተሪንግና የትንተና ስራ በመስራት ስለተቋሙ በቀረቡ አሉታዊና አወንታዊ ዘገባዎችን መለየት፣ማደረጀትና ዝንባሌዉን መተንተን፤
- የቀረቡ አታዊ ዘገባዎችን በመተንተን ለበላይ አመራር በመቅረብ በሚሰጠዉ ግብረመልስ ላይ ተወያይቶ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፤
- በተቋሙ ላይ በቀረቡ አሉታዊ መልዕክቶች ላይ ህብረተሰቡ እውነታውን እንዲረዳ ፈጣን ግብረ መልስ በመስጠት የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፤

- ህብረተሰቡ እዉነታዉን እንዲረዳ በተከታታይ መረጃዉን በማሰራጨት አሉታዊ ዘገባዎችን ማስተካከል ስራ መስራት፤
- ስለተቋሙ ሰፊዉ ተደራሽ መረጃ እንዲኖረዉ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ኮንትራት ዉል በመፈፀም መረጃዎችን መሰራጨት፤

**ግብ 4፡- በየሩብ ዓመቱ ከህዝብ ክንፍ፣ ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ክልሎች እና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጋር የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት በአዋጅ ቁጥር በ621/2001፣በደንቡ ቁጥር 168/2001 እና በመመሪያዎች፣ማኑዋሎችና ቅጾች እና በፀረ ሙስና ህግ ላይ የተለያዩ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ደንበኞችንና የባላድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማሳደግ ለህጉ ተፈፃሚነት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ከኤጀንሲው የህዝብ ክንፍ ጋር መደበኛ የምክክር መድረክ መፍጠር፤
- ተገልጋዮች በአመለካከት፣ በአደረጃጀትና በአሰራር ዙሪያ ያሉባቸዉን ችግሮች መለየት፤
- የምክክር መደረክ ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን በጀትና ሎጂስቲክ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤
- በምክክር መድረኩ ላይ የሚሣተፉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መለየት፤
- በምክክር መድረኩ ላይ የሚገኙ የዘርፍ አስተዳዳሪዎችን እና የክልል ቢሮዎችን መለየት፤
- ለክህዝብ ክንፍ፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም ለባለድርሻ አካላት በአዋጁ፣ በደንቡና በተዘጋጁ፤ መመሪያዎች፣ በፀረ ሙስና ህግ እና በሥራ አፈፃፀም ዙሪያ የምክክር መድረኮች ማዘጋጀትና ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ መፍጠር፤
- ዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ከክልሎች በአዋጁ ላይ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተረድተው ከተቋሙ ጋር በቅንጅት በመስራት የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት እንዲቻል የመግባቢያ ሰነድ መዳበርና መፅደቅ፤
- በተደረኩ የምክክር መድረኮችና ስልጠናዎች የተሰበሰቡ ግብዓቶችን በመጠቀም ያሉ ችግሮች መፍታት፣

**ግብ 5፡- የኤጀንሲውን የመረጃ ቋት እና ድረ-ገጽ አስፈላጊ መረጃዎችን በሚይዝ መልኩ አሻሽሎ መገንባት፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የተቋሙ ዳታ ቤዝ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን መስጠት በሚችል ሁኔታ እንደገና እንዲገነባ ማድረግ፤
- የኤጀንሲውን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በየጊዜው አደራጅቶ ጥራት ያለው መረጃ በመረጃ ማዕከል (Central Data Base) አደራጅቶ መያዝ፤
- የተቋሙን ድረ-ገጽ ደረጃውን በማሳደግ የተለያዩ መረጃዎችን በየጊዜው መጫን፤

- በተለያየ ምክንያት የተዘጉና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸውን በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት መረጃ መያዝ፤
- የፈቃድ ዕድሳት ያደረጉትንና ያላደረጉትን ድርጅቶች መረጃ በመለየት መያዝ፤
- ለደንበኞች የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎችን ሲጠይቁ በሶፍት ኮፒ፣ በሃርድ ኮፒና በኢሜል በመላክ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ፣
- የሰርቨር እና ወርክስቴሽኖች ኮምፒተሮች ፕሪንተሮች እና የኔትወርክ ሚዲያዎችን ብልሽት ሲደርስባቸው በወቅቱ ጥገና ማድረግ፣
- Wide Area Network(WAN)፤የLocal Area Network(LAN) እና የድረ-ገጽ አገልግሎቱ ስራውን በትክክል እየሰራ መሆኑን መከታተል፤

**ግብ 3:- የሪከርድና ማኅደር አያያዝን ዘመናዊ በማድረግ የኤጀንሲውን መዝገብ ቤት የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ማጎልበት፤**

**ዝርዝር ተግባር**

- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ፋይሎች በዳታ ቤዝ አደራጅቶ መያዝ፤
- የመዝገብ ቤቱ አገልግሎት አሰጣጥ ደንበኞችን ያረካ እንዲሆን በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የነባርም ሆነ የሚቀጠሩ ሠራተኞችን ማኅደሮች አሟልቶ መያዝ፤
- የሰው ሀይል መረጃ ወቅታዊ ሆኖ እንዲደራጅ ማድረግ፤

## 2.2.6. የዕቅድ፣ ፋይናንስና ግዥ ማጠናከር

**ዓላማ:- በዕቅድ የተመራ ወጪ ቆጣቢ፣ ጥራት ያለው፣ ፈጣን፣ ተደራሽና ውጤታማ የሆነ የአገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፤**

ግብ 1:- የወጪና የገቢ ሂሳቦችን መደብ በመለየትና በመመዝገብ የሂሳብ ሚዛን በመስራት ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ፤

- የሂሳብ ሰነዶችና ቅፆችን በማዘጋጀት ተሰብሳቢ ሂሳቦችንና ተከፋይ እዳዎችን የአደራ ሂሳቦችንና ሌሎችን ለይቶ መመዝገብ፤
- ዝርዝር ሂሳቦችን በTR, በGL, በSL, በIBEX ሶፍት ዌር መስራት፤
- በየቀኑ የሚከናወኑ ተግባራትን መዝግቦ ከወጪ ቀሪ በማመዛዘን እለታዊ ሪፖርት ማድረግ፤
- በየወሩ መጨረሻ ለሪፖርት የተዘጋጀ ባላንስ በማምጣት ወርሃዊ የሂሳብ ዝርዝር ሪፖርት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መላክ፡፡

ግብ 2:- ጥራትና ፍጥነት ያለው አሰራር በመፍጠር ክፍያዎች እና ፈሰስ የሚደረጉ ሂሳቦችን በወቅቱና በጥራት በማከናወን አገልግሎት አሰጣጣችን በማሻሻል የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ፤

## ዝርዝር ተግባራት

- የሰራተኛውን ደመወዝ በባንክ በኩል  በወቅቱ መክፈል፣
- የአገልግሎት፣ የክቃ □□ ፣ የውልና የቢል ክፍያዎችን በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ክፍያ መፈፀም፤
- ከእቃና አገልግሎት ግዥ የሚሰበሰቡትን VAT እና with holding tax በመሰብሰብ በየወሩ ለገቢዎችና ጉምሩክ ማስገባት፤
- ከምዝገባና ከሌሎች አገልግሎት ብር 700,000.00 በመሰብሰብ በየወሩ ለ/ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ማእከላዊ ግምጃቤት ማስገባት፤

## ግብ 3፡- በእቅድና በበጀት የተደገፉ የተለያዩ ግዥዎች ወጪ ቆጣቢ፣ጥራት ያለው፣ፈጣን፣ ተደራሽና የተገልጋዩን እርካታ ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ፤

## ዝርዝር ተግባራት

- ሁሉም ዳይሬክቶርቶችና ቡድኖች የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ያቀረቡትን የግዥ ፍላጎት በመለየትና ማቀናጀት አጠቃላይ በመስሪጸ ቤቱ □ሚያስፈልጉ መገልገያ ዕቃዎችን አይነትና ፍላጐት ማጥናት፤
- የተቋሙን የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- □ቅታዊ የሆነ የገበያ ጥናት በማድረግ ለሚገዙ መገልገያ ቁሳቁሶች ጥራት ያለው □ክቃ □ር□ር መግለጫ /Specification/ ማዘጋጀት፤
- የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት ተጫራቾችን በማወዳደርና በመምረጥ የጨረታውን ውጤት በማፀደቅ ከአሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶች በውል መሰረት ወቅታዊ ግዥ መፈፀም፤
- በፕሮፎርማ ለሚገዙ ዕቃዎች ፕሮፎርማ በመልቀም፣ በማወዳደር እና በመምረጥ ግዥ መፈፀም፣

## ግብ 4፡- ፕሮግራም በጀትን ተግባራዊ በማድረግ የበጀት አጠቃቀማችንን ማሳደግ፤

## ዝርዝር ተግባራት

- ለ2008 በጀት አመት የፀደቀውን የበጀት ፕሮፖዛል በበጀት መጠየቂያ ቅጽ በማዘጋጀት ከነደጋፊ ሰነዱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መላክ፤
- የፀደቀውን  በጀት በየስራ ሂደቱ መደልደልና ማሳወቅ፣
- በ□□ሩና በየሶስት ወሩ የካሽ ፍሎው መጠየቂያ ቅፅ በማዘጋጀት ለስራ ማስኬጃ የሚያስፈልግ □ብር መጠን ካሽ ፍሎው አዘጋጅቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መላክ፤

- የኤጀንሲውን ፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ከውጤት ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ወቅታዊ የሆነ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በየሶስት ወሩ ፕሮግራም በጀት የዕቅድ አፈፃፀም አዘጋጅቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መላክ፤
- የበጀት አመቱን የስድስት ወር የበጀት አፈፃፀም በመገምገም እጥረት ያለበትን የስራ መደብ መለየት፤
- በመጀመሪያው በጀት አመት ያልታቀዱና በጀት ያልተያዘላቸውን ወሳኝ ለሆኑ ስራዎች ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ ማስፈፀም፤
- በጀትን በአግባቡ መጠቀምና ዕጥረት ያለባቸውን መደቦች በመለየት የበጀት ዝውውር ማድረግ፤
- የ2008 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም በመገምገም፣ የተቋሙን ስትራቴጅክ ዕቅድ እና የዳይሬክቶሬቶችን የበጀት ጥያቄ መሰረት በማድረግ የ2009 በጀት ዓመት ኘሮግራሚንግ በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- የተዘጋጀውን የበጀት ፕሮፖዛል የበላይ ሀላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግና በማስተካከል በኃላፊዎች በማፀደቅ በወቅቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መላክ፤

## ግብ 5፡- የኤጀንሲውን የፊዚካል ዕቅድ ወቅቱን ጠብቆ በማዘጋጀት፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የዕቅድ አፈፃፀሙን ወደላቀ ደረጃ በማሳደግ ወቅቱን የጠበቀ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ስርአት እንዲኖር ማድረግ፣

### ዝርዝር ተግባራት

- ለ2008 በጀት ዓመት  የመጀመሪያ ግማሽ አመት የዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም የ6 ወር የተከለሰ ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- ወቅቱን የጠበቀ የኤጀንሲውን ወርሐዊ፣ የሶስት ወር፣ የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ከዕቅድ ጋር በማገናዘብ የተጠቃለለ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት፣
- በክትትል የተገኙ መረጃዎችን በማጠናቀር፣ በመተንተን፣ በማደራጀት እና ያልተሰሩ ስራዎችን ትኩረት በመስጠትና በመለየት እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ ግብረ መልስ መስጠት፣
- የ2008 በጀት አመት የዕቅድ አፈፃፀም በመገምገምና የዳይሬክቶሬቶች ዕቅድና የ2ኛውን ዙር ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የ2009 በጀት አመት የተቋሙን ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- የተዘጋጀውን ረቂቅ ዕቅድ ለበላይ አመራር በማስገምገም በተሰጠው ግብዓት መሰረት በማስተካከል ዕቅዱን ማፀደቅና ለሚመለከተው አካል መላክ፣

## 2.2.7. የንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት፤

**ዓላማ፡-ወጪ ቆጣቢ፣ጥራት ያለው፣ ተደራሽና ውጤታማ የሆነ የንብረት አስተዳደርና የጠቅላላ አገልግሎት እንዲኖር በማድረግ ተቋሙ ያቀዳቸውን ግቦች እንዲያሳካ ድጋፍ መስጠት፤**

**ግብ 1፡- የንብረት አጠቃቀም፣ አጠባበቅና ስርጭት ህግና ስርዓትን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ የኤጀንሲዉ ንብረት ለተገቢው አገልግሎት እንዲውል ማድረግ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የተገዙ ዕቃዎች በታዘዘው ጥራትና ብዛት መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ በፍጥነት ገቢ በማድረግ ለተ□ቃሚ□ በፍጥነት ማሰራጨት፤
- የቋሚ ንብረቶች ምዝገባና ቆጠራ በማድረግ ኮድ መስጠት፤
- አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችን በመለየት እንዲወገዱ ማድገግ
- ከወጪ ቀሪ ንብረቶችን ወርሃዊ ሪፖርት ማጋጀት፤
- የተበላሹ ንብረቶች በወቅቱ እንዲጠገኑ ማድረግ፤
- የኤጀንሲውን ንብረት ህንፃውን ጭምር ደህንነቱንና ጽዳቱን በመጠበቅ የተመቸ የስራ ሁኔታ መፍጠር።

**ግብ 2፡- የተሽከርካሪ ነዳጅ እደላ እና ስምሪት ወጪ ቆጣቢና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ፤**

- የተሻለ የነዳጅ አጠቃቀምና ስልት እጥንቶ ለውሳኔ ማቅረብ፣
- ተሽከርካሪዎች የሚሄዱበት ኪሎ ሜትርና በማስለካት በልኬቱ መሰረት የተጠቀሙት የነዳጅ መጠን በመለካትና በመከታተል መረጃዎችን በመተንተን አፈፃፀመን በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ፤
- ቋሚ እቃዎችና ተሽከርካሪዎች ሲበላሹ በአፋጣኝ ጥገና ማድረግ እንዲሁም ለተሽከርካሪ በ5000 ኪ.ሜ ዘይት መቀየር እና 10000 ኪ.ሜ ፍተሻና አጠቃላይ ሰርቪስ ማድረግ፤
- ተሽከርካሪዎችን እንደየስራ ባህሪ መደልደልና ለስራ ዝግጁ ማድረግ፤
- ለተቋሙ ተጨማሪ ተሽከርካሪ እንዲመደብ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ማስመደብ፤

## 2.2.7 የውስጥ ኦዲት አገልግሎትን ማጠናከር

**ዓላማ፡- የተዘረጋውን የቁጥጥር ሥርዓት በማጠናከር የመንግስት ሃብትና ንብረት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በማድረግ የሀብት ብክነትን ማስወገድ፤**

**ግብ 1፡- የፋይናንስ አስተዳደርና ስርዓቱ በመመሪያና ደንብ መሰረት ግልፅ፣ ወጪ፣ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን የፋይናንሻል ኦዲት ምርመራ በማከናወን አፈፃፀሙን 100% ማሳደግ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የጥሬ ገንዘብ፣ የባንክ ሂሳብን ከሌዥር ከባንክ እስቴትመንት ከወጪ ማስረጃዎች ጋር መናበቡን ማረጋገጥ፤
- በፋይናንሻል ኦዲት  የገቢ ሂሳብ፣ የወጪ ሂሳብ፣ የደረሰኝ፣ የሂሳብ ሪፖርቶች፣ ሌጀሮች፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ፣ የዝውውር ሂሳቦችን ትክክለኛነት በኦዲት ምርመራ በማረጋገጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፤
- የኦዲት ግኝቶች ላይ መታረምና መስተካከል ያለባቸውን ለወደፊቱ እንዲስተካከሉ ሙያዊ አስተያየትና ምክር በመስጠት መስተካከላቸውን ክትትል ማድረግ፤
- ኦዲቱ ሲጠናቀቅ ደረጃውን የጠበቀ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ መላክ፣

**ግብ 2፡- የተቋሙ የንብረት አያያዝ በወጡ ህጎች፣ ደንቦችንና መመሪያዎች መሰረት የተያዘ መሆኑን በኦዲት በማረጋገጥ አፈፃፀሙን 97% ማሳደግ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የኤጀንሲው አጠቃላይ የቋሚና አላቂ ንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያን የተከተለ አፈፃፀም መኖሩን በኦዲት ማረጋገጥ፤
- የተሽከርካሪ አያያዝ አጠባበቅና አጠቃቀም፣ የነዳጅ አሞላል፣ የኩፖን አያያዝና አወጣጥ በስቶክ ማኔጅመንት ስርአት መሰረት መሆኑን በኦዲት ማረጋገጥ፤
- አጠቃላይ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በስቶክ ማኔጅመንት ስርአት የተከተለ መሆኑን በኦዲት ምርመራ በማረጋገጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፤
- አፈፃፀሞች ውጤታማ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሙያዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፤
- በኦዲቱ ዙሪያ በተገኙ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ ከኦዲት ተደራጊዎችና ከሚመለከታቸው ጋር በማድረግ የጋራ ግንዛቤ በመያዝ አፈፃፀሙን መከታተል፤

**ግብ 3፡- በተቋሙ የሚፈፀሙ ግዥዎች በእቅድና በፕሮግራም እንዲሁም በመመሪያ መሰረት የተፈፀሙ መሆናቸውን በኦዲት ማረጋገጥ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የተፈጸሙ ጥቅል ግዥዎች የመንግስት የግዥ መመሪያን የጠበቁ መሆናቸውን በኦዲት ምርመራ ማረጋገጥ፤
- የተገዛው እቃ ወደ ንብረት ክፍል መግባቱንና ስርጭቱ በስቶክ ማኔጅመንት ስርአት መሰረት መፈፀሙን በኦዲት ማረጋገጥ፤
- የኦዲት መግቢያና መውጫ ስብሰባ በማድረግ ከተመርማሪዎች ጋር በመተማመንና ማሻሻዎችን በመስጠት የኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀትና ማሰራጨት፡፡

**ግብ 2፡- የኤጀንሲውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የተገልጋዩንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ያሟላ መሆኑን የክዋኔ ኦዲት በማድረግ የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- አጠቃላይ የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ  በመፈተሽ ለክዋኔ ኦዲት መነሻ የሚሆን የዳሰሳ ጥናት ማድረግ፤
- በጥናቱ መሰረት የክዋኔ ኦዲት የሚደረግባቸውን ዳይሬክቶሬቶች ወይም ቡድኖች በመለየት የክዋኔ ኦዲት ማድረግ፤
- በማንኛውም ሁኔታ ያሉ ግኝቶችን እንዲሁም የክፍተቱን መንስኤ መዝግቦ በመያዝ ከሚመለከታቸው ጋር መተማመን፤
- በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ዙሪያ የተሟላ መረጃ በመያዝ ለተገኙ ያሰራር ክፍተቶች ወይም ግኝቶች ከነመፍትሄው  ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለተው አካል መላክ፤
- በክዋኔ ኦዲት ወቅት የተገኙ ግኝቶች መስተካከላቸውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙን መከታተል፤

## 2.2.8. የሰው ኃብት ልማት *ተግባራት ማከናወን፣*

**ዓላማ :- ኤጀንሲውን ጥራትና ብቃት ባለው የሰው ሀይል በማደራጀት  የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ፤**

**ግብ1:- ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በዝውውር በማሟላት የተቋሙን የመፈፀም አቅም** ማሳደግ፤

**ዝርዝር ተግባር**

- የተቋሙን የቅጥር፣ የደረጃ እድገትና የዝውውር መመሪያን ማዘጋጀት፤
- አዲስ ለሚፈቀድ መደብና በየጊዜው ከኤጀንሲው ለሚለቁ ሰራተኞች ምትክ በዕድገትና በቅጥር ማሟላት፤
- የተወዳዳሪዎችን ዶክመንት ጥንቃቄ ባለው መልኩ በመለየት የጽሁፍና የቃል ፈተና በመስጠትና ፈተናውን ያለፉትን ሰራተኞች የቅጥር ፎርማሊቲ በሟሟላት በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት ቅጥር መፈፀም፤
- አዳዲስ ለሚቀጠሩ ሰራተኞች የተመደቡበትን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በፅሑፍ በመስጠት እና ተገቢ ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ፤
- የደረጃ እድገትም ይሁን የቅጥር ሂደት በተቀላጠፈና ጥራት ባለዉ መልኩ በጊዜ ሰሌዳ መፈጸም፤
- ነባርና አዳዲስ የስራ መደቦችን በመፈተሽና በማጥናት በማስፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

**ግብ 2፡- ለአመራር ሰራተኛው ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠርና የተቀላጠፈና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፤**

**ዝርዝር ተግባር**

- በሲቪል ሰርቪስ ህግ ዙሪያ ለተቋሙ ሰራተኞች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ በመከናወን ሰራተኛዉ መብትና ግዴታዉን እንዲያዉቅ ማድረግ፤
- ለሰራተኛው ምቹ የስራ ቦታ /የሰርቪስ፣የመዝናኛ፣የጤና፣የስራ ሁኔታ፣...ሌላም /እንዲሟሉና እንዲመቻቹ ማድረግ፤
- በሰራተኛው ዙሪያ የህግ ጥሰቶችን እንዲስተካከሉ በህጉ መሰረት የዲስፕሊንና ቅሬታ ኮሚቴዎችን አወቃቀርና አፈጻጸምን በመከታተል የተቋሙ ይሁን የሰራተኛው መብት እንዲከበር ማድረግ፤
- የአመራርና የሰራተኛው የአመት ፍቃድ በእቅድ እንዲመራና እዲፈጸም ማድረግ፤
- ሁሉም ሰራተኛ የጡረታ ቁጥር እንዲያገኝ ማድረግ፤
- በሰራተኞች የሚጠየቁ አገልግሎቶች በጥራትና ቅልጥፍና መስጠት፤

## 2.2.9. የሴቶች፣ ህፃናትና የወጣቶችን ጉዳይ

**ዓላማ፡- በኤጀንሲው ውስጥ የሴቶችና ወጣቶችን ተሣትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በራሣቸው የሚተማመኑና የላቀ አስተዋጽኦ የሚያስመዘግቡ ሴቶችና ወጣቶችን ማፍራት፡፡**

**ግብ 1፡- የሥርዓተ ጾታ እኩልነት፣ የሴቶችና የወጣቶችን ተሣታፊነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን በማከናወን የለውጥ ኃይል የሚሆኑ ሴቶችና ወጣቶችን መገንባት፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ዳይሬክቶሬቶችና ቡድኖች ሥርዓተ ፆታን የዕቅዳቸው አካል አድርገው ማቀዳቸውን መከታተል፤
- የተቋሙን ሴት ሠራተኞች ፎረም ድጋፍ በመስጠት ማጠናከር፤
- የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ሥርዓተ ፆታን ማካታተቸውን እንዲሁም የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ፆታን ያማከሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- በማስፈፀሚያ ማዕቀፎች በአለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች፣ ፖሊሲዎች፣ ሰነዶችና ቻርተሮች በኤጀንሲውና በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሰርጽ ማድረግ፤
- በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ላይ የሚሰሩ የፌደራልና የክልል መንግስት መስሪያቤቶች ጋር በቅንጅት መስራት፤
- ከተገልጋዮች፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከአጋር ድርጅቶችና ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ጋር በኢንተርፌስና በቅንጅት የሚሠሩ ሥራዎችን ማስተባበር፤

- በተቋሙ ውስጥ በሚከናወኑ የቅጥር የዝውውርና የደረጃ ዕድገት ተግባራት ውስጥ ሴቶች የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፤
- በሴቶችና በወጣቶች ተጠቃሚነት ላይ የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ እንደተቋማችን ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ በመፍጠር ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

**ግብ 2፡- በሴቶች & ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዙሪያ ግንዛቤ ያለውና አቅሙ የተገነባ ሠራተኛን መፍጠር& □ር□ር ተ□ባር**

- ለሴቶችና ወጣቶች የአቅም ማሳደግ የሚያስችሉ የአጭር፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ስልጠና ማፈላለግ፤
- ለኤጀንሲው ሴቶችና ወጣት ሰራተኞች በራስ የመተማመን ስሜታቸውን እንዲያጐለብቱ በAssertiveness ላይ ስልጠና መስጠት፤
- ለኤጀንሲው ሠራተኞች በጀንደር ሜኒስሪሚንግና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሥልጠና መድረክ ማመቻቸት፤
- በተቋሙ ውስጥ የሴቶች፣ የህፃናትና የወጣቶችን ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ በዓላት በማክበር ግንዛቤና ንቅናቄ መፍጠር፤
- በኤጀንሲዉ ሴትና በወጣት ሰራተኞች በጎጂ ልማዳዊ ድርጊትና በመጤ ባህል ዙሪያ የግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ሴቶች በሥነተዋልዶ ጤና ዙሪያ የግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- የኤጀንሲው ሴት ሠራተኞች ፎረም አመራሮች በትራንስፎርሜሽናል ሊደር ሽፕ ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤

## 2.2.10. የኤጀንሲውን ዘርፈ ብዙ ተግባራት

### 2.2.10.1 □□.□□□□ □□□□□□

**ዓላማ፡- የኤጀንሲው ሠራተኞች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ የሚያመጣውን ጉዳት ተገንዝበው እራሳቸውንና ማህበረሰቡን በመጠበቅ በኩል የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ፡፡**

ግብ1፡- **ለኤጀንሲው ሰራተኞችና ባለሙያዎች በ**HIV/AIDS **በቅድመ መከላከል ዙሪያ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማመቻቸት ህሙማንን ባለማግለልና በኤች.አይቪ.ኤድስ ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፤**

**□ር□ር ተ□ባር**

- ለኤጀንሲው ሠራተኞች በቅድመ መከላከል ዙሪያ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤያቸውን ማሣደግ፤
- በተቋሙ አዲስ የሚቀጠሩም ሆነ ነባር ሰራተኞች ኤች. አይ. ቪ. .ኤድስ በደማቸው መኖሩን ያሣወቁ ህሙማን በቅጥር& በዝውውርና በደረጃ ዕድገት ወቅት ባለማግለል የዜግነት መብታቸው መጠበቁን መከታተል፤
- የኤጀንሲው ሠራተኞች በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- የኤጀንሲው ሠራተኞች በሥራ ቦታም ሆነ በመሥክ ሥራ ላይ ለኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ያላቸውን ተጋላጭነት የዳሰሳ ጥናት ማካሄት፤
- ዓለም አቀፍ የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ቀን በዓልን በማክበር ግንዛቤና ንቅናቄን መፍጠር፤
- የኤጀንሲው ሠራተኞች እራሣቸውን ከኤች.አይ.ቪ ኤድስና ከአባለዘር በሽታዎች እንዲከላከሉ ያልተቋረጠ የኮንዶም ሥርጭት ማካሄድ፤
- ከኤጀንሲው መደበኛ በጀት እንዲመደብ ማድረግና ተፈጻሚነቱን በመከታተል ሥራ ላ□ ማዋል፤
- በ2006 ዓ.ም የተጀመረው የ2 ህፃናት ድጋፍና □እንክብካቤ ተግባራት ሣይቋራረጥ ድጋÕ እንዲቀጥል ማድረግና የህፃናቶቹን የትምህርትና የኑሮ ሁኔታ መከታተል፤
- የኤች.አይ.ቪ ሜኒስትሪሚንግ በተቋሙ ውስጥ ያመጣውን የግንዛቤ ለውጥ ጥናት ማካሄት&
- ተመሣሣይ የመንግሥት ተቋማት የኤች አይ ቪ ኤድስ ሜኒስትሪሚንግና የድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት የአፈጻጸም ሁኔታ መልካም ተሞ□ሮ ካላቸው ተቋማት የልምድ ልውውጥ በማድረግ መልካም ተሞክሮዎችን ወደ ኤጀንሲው በማምጣት መተግበር፤
- በኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

**2.2.10.2 □□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□□□**

**ዓላማ፡- የተፈጥሮ ሀብት ብክነት በሀገራችን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ የሚያመጣውን ጉዳት ለመቀነስ እንዲቻል በዘርፉ የተሰማሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ድጋፍ ማድረግ፤**

**ግብ 1፡- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤን ማሳደግ፤**

**□ር□ር ተ□ባር**

- በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የሚሰሩ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን ልዩ ትኩረት በመስጠት ድጋፍና ክትትል በማድረግ የሀገራችንን የአየር ብክለት እንዲቀንስ ጥረት ማድረግ፤
- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦታ በመውሰድ በተቋሙ ስም ችግኝ በመትከል በቀጣይ እንክብካቤ ማድረግ፤

## ክፍል ሦስት

### 3.1. የክትትል፣ ድጋፍ እና የግንኙነት ሥርዓት

ኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በብቃት ለመወጣት እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ በላቀ ሁኔታ መፈፀም እንዲችል ወቅታዊና ሥራ ተኮር ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ በማድረግ በየጊዜው የማስተካከያ እርምጃዎችን የመውሰድ ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የክትትል፣ድጋፍና ግንኙነት ሥርዓቱ በሚከተለው አግባብ ይፈፀማል፡፡

- ❖ የለውጥ ሰራዊት ግንባታ መርሆችን በመከተል ሰራተኛውን በክህሎትና በአመለካከት የማብቃት ስራ የተከተለ ይሆናል፡፡
- ❖ የየዳይሬክቶሬቱ ኦፊሰሮች፣ ባለሙያዎችና ሠራተኞች ከስራ ሂደቱ ዕቅድ በመነሳት የ2008 ዕቅዳቸውን፣ በየሩብ አመት፣ በየወር እና በየሳምንት ዕቅድ በማውጣት ለዳይሬክቶሬቶቹ ወይም ለቡድን መሪ ያቀርባሉ፡፡
- ❖ በየደረጃው የሚመለከተው ኃላፊ በተቋሙ የወጡትን አሰራሮችና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ ሥራዎች የተከናወኑ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ወቅታዊ የሆነ አፋጣኝ መፍትሔ ይሰጥባቸዋል፡፡
- ❖ ሁሉም ዳይሬክቶሬቶችና ቡድኖች በስራቸው ያሉ ሠራተኞች ያከናወኑዋቸውን ተግባራት ጥራት ያለው መረጃ እየተያዘ መሆኑን ከስር ከስር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ያረጋግጣሉ፡፡
- ❖ የሁሉም ዳይሬክቶሬቶች ሠራተኞች በዳይሬክቶሬቱ ሰብሳቢነት በየሳምንቱ ዓርብ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እንዲሁም የመረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡ ዳይሬክቶሬቶች በየ15 ቀኑ አጭር ሪፖርት አጠናቅረው ለዋና ወይም ም/ክ ዳይሬክተሩ ያቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም የስራ አመራር ካውንስሉ ተሰብስቦ ተቋማዊ መፍትሔዎችን ያስቀምጣል የተቀመጡ መፍትሔዎች ወደፈፃሚው ሳይሸራረፉ እንዲያወርዱ ይደረጋል፡፡
- ❖ ለክትትል ተግባር ወደ መስክ የሚሠማሩ ኦፊሰሮች ያሉበትን ሁኔታ በስልክ ለዳይሬክቶሬቱ ያሳውቃሉ፤ ሲመለሱ ሙሉ የፅሁፍ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡
- ❖ በዳይሬክቶሬቱና አጠቃላይ በተቋም ደረጃ በየወር፣ በየ3 ወሩ፣ በየ6 ወር፣ በየ9 ወር እና የዓመቱ ማጠቃለያ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና ግምገማ ወቅታቸውን ጠብቀው ይከናወናሉ፡፡